# አስተያየት – በሌተናል ጄኔራል ፃድቃን ገ/ትንሳኤ ሃሳቦች ዙሪያ

July 26, 2016

በመጀመሪያ አገር ሰላም አይደለም ብለው በመነሳት ችግሩን፡ወደችግሩ ያመሩንን ምክንያቶች፡ሊከተሉ የሚችሉትን ኩነቶች፡ በችግሩ አፈጣጠርም ሆነ በሰነዘሯቸው መፍትሄ ያሳቦች ዙሪያ ሚናቸው የጎላ ነው ብለው በሚያስቧቸው ሃይሎች የሁኔታ ትንተና በማድረግ ማድረግ የሚገባቸውን በግልፅ በማቅረብዎ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ስብሃት ነጋ የተቆጣ ግለሰብ እንጅ የተከፋ ህዝብ የለም ባለበት አገር፡ ብዙውን ጊዜ ስለ ትምክህትና ጥበት （አማራና ኦሮሞ）እንጂ ሰለ ዋናው ችግር ፈጣሪ ትችት ሲቀርብ በማንሰማበት አገር፡ ዘመነ ጥጋብ ከሆነበት መንደር ዘመነ ችግርን የሚያስታውስ ፡ትግራይ የምትባል የኢትዮጵያዊነት ምልክትን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ከሚተጋ ድርጅት የወጣ ግለሰብ ስለ ኢትዮጵያ ተጠቦ ይህን መጻፉ በራሱ ትልቅ ጉዳይ ነው። ከጠላቶቻችን ጋር አብሮ ሊያስመታን ነው የሚል ትችት እንደሚመጣብዎትም ተገንዝበው ይምጣ ብለው ያደረጉት ነው ብዬም አምናለሁ። በዚም አከብርዎታለሁ። በችግሩና በችግሩ አፈታት ባቀረቧቸው ሃሳቦች ዙሪያ ብዙም የልዩነት ሃሳብ የለኝም። የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በተመለከተ ግን በአንድ አማራ ወይም ኦሮሞ እግር ቆሞ ማዬትን ሰለሚጠይቅ እንዲያዩትም ሰለምፈልግ የሚሰማኝን ማካፈል እፈልጋለሁ።

1）በኔም ሆነ በአብዛኛው አማራና ኦሮሞ እምነት ትግራይ፡ መከላከያ፡ ደህንነት፡ ፌደራል ፖሊስ ፡ እና ፌደራል መንግስት በስም ካልሆነ በቀር በይዘት አንድ ናቸው። ሁሉም የወያኔ ተቋሞች ናቸው። ወያኔን ያገለግላሉ ሌላውን ይገዛሉ።

2）ትግራይና ተጠቃሚነት። የትግራይ ህዝብ እንደሌላው ህዝብ የታፈነ ቢሆንም በስርአቱ በተለዬ አልተጠቀመም ብዬ አላስብም። በመሰረተ ልማት በሃብት ክፍፍል ቀመር （ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚገኝ）በመንግስት፡ በንግድ፡ በሁሉም መስክ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታዎቅ ደረጃ ለትግራይና ለተዎላጆቿ ያዘነበለ ነው። ይህ ደግሞ ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ የነበረና እያደገ የመጣ እንጂ በአንድ ዎቅት ብቅ ያለ ወይም እዬከሰመ የሄደ ድርጊት አይደለም። ይህ የልዩ ተጠቃሚነት መንፈስ በትግራይ ኢሊት ውስጥ በመስረጹ ስርአቱ ሳይቀዬር እንዳለ እንዲቀጥል ይፈለጋሉ።

3） ለኔ አሁን ባለው የ TPLF አገዛዝና Fascism መካከል ልዩነቱ ጎልቶ አይታዬኝም። ይህ አገላለጽ የተጋነነ ሊመስል ይችላል። የፋሺዝምን ስልታዊ ባህሪዎች በመዘርዘር ሃሳቤን ላስረዳ፡

1. ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ህብረተሰብን በብሄሩ ማነሳሳት

2. ሰባዊ መብቶችን መደፍጠጥ

3. የራስ ብሄር ያለ ለዩነት እንደ አንድ ሰው እንዲያስብና እንዲነሳ “ይሂ ብሄር ሊያጠፋህ ነው” በሚል ሌላዎን ብሄር መፈረጅና ማጥላላት

4. የበላይነትን በዎታደራዊ መንገድ ማረጋገጥ

5. መገናኛ ብዙሃንን ተቆጣጥሮ የራስን አስተሳሰብ ማስረጫ ማድረግ

6. የሃገር ደህንነትን ለአላማ ማስፈጸሚያ አጣሞ መተርጎም （የሸብር ህጉን ያስተውሏል}

7. ሃይማኖትን ሳይቀር በመቆጣጠር ለአላማ ማስፈጸሚያ ማድረግ

8. የይስሙላ ምርጫዎቹን ማካሄድ

9. ጠላት ብለው የፈረጁትን በጅምላ መቅጣት ዎዳጅ ያሉትን በጅምላ መጥቀም

10. መረን የለቀቀ የእከከኝ ልከክልህ ግኑኝነትና ሙሰና ናቸው::

ከነዚህ ውስጥ የቱ ነው የዎያኔ መመሪያ ያልሆነው？　ምንም! ስለዚህ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በፋሽዝም ስር እንዳለሁ ይሰማኛል። ፉሽዝም ከትግራይ ይመጣል ብለን ባለመጠበቃችንና እያደሩ እዬበሰሉ ይሄዳሉ ብለን በማሰባችን በዙም የዎያኔ አስተዳደር የፉሽዝም አስተዳደር ሆኖ አይሰማንም ነበር። አሁን ግን እንኳን ለኛ ለዎያኔ ለራሱ የማይደብቀው ደረጃ ደርሷል። ታስርህ ሳይቀር በዘርህ ብቻ የተለዬ ሰቆቃ የሚፈጽም ስርአት ነው የሚገዛን።

4）ሊበራል/ልማታዊ መንግስትን በተመለከተ እምነቲ እንደ ጸሃፊው ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ አተገባበሩ ግን ከሁቱም ያልሆነ እንዴውም ወደ ፋሺዝም ያደላ የመንግስት ስርአት ነው ያለው። ሃገራዊ ሃብትን በፍጥነት ወደ አንድ ክልል ሃብት ያዛዎረ፡ ሃብት የማፍራቱም ሆነ ክፍፍሉ ክአንድ ብሄር ለዎጡ ሰዎች የሚያዳላ ስርአት “ለማታዊ” ነኝ ማለት ከማታለል ያለፈ ነገር አይሆንም። የኮርያ ሳምሰንግ ወይም ደዉ የመላ ኮሪያዊያን እንጅ የአንድ ቢሄረሰብ ካምፓኒ አይደለም። የልማታዊው መንግስት ውጤት የሆነው ኢፈርት የትግራይ እንጅ የሌላው ኢትዮጵያዊ አየደለም። ሌላው ክልልም ይህን ማድረግ ይችላል የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ ይችላል። ባጭሩ ሌሎች የሚፈቅድላቼው “አለሁ” እንዲሉ እንጅ እንዲኖሩ አይደለም። አቅም የሚፈጠረው አንዱን ብሄር መሪ ሌላውን ተመሪ ለማድረግ ባለመ ነው። ለምሳሌ የአማራ ህዝብ የሚመራው ብሩህና አቅም ባላቼው ለጆቹ ሳይሆን በዝቃጮች ወይም በሌላ ብሄር ነው። አቅም ያላቸው ትምክተኛ እየተባሉ የሳደዳሉ። የባንክ ብድርም ሆነ መሬት ለማግኘት ፕሮጀክትህን ከተጋሩ ጋር ተጣምደህ ካላቀረብክ አንድ ኢንች አትራመድም። ተበደልኩ ወይም ጥያቄ አለኝ ማለት እስር ቤት ያስገባል።ዎያኔ ልማታዊ መንግስት ሳይሆን ፋሺስት ነው። የዛሬ 25 አመት የነበረው ህልም ዛሬ የለም።

5）　መፍትሄ ሃሳቦች ላይ፡ በተለይ ለአማራና ለኦሮሞ አሁን ያለንበት ሁኒታ በዚህ መልክ ከቀጠል አብሮ ለመኖርም ሆነ ለመለያዬት የግድ ጦርነት ውስጥ መግባት አንዳለብን አስገንዝቦናል። መንገዱንም ጀምረናል። ተዋርዶ ለመኖር ዝግጁ አይደለንም። ወያኔም ሆነ የትግራይ ኢሊት ያከልካይ ከመዝረፍ ውጭ ያለውን አማራጭን “ወድ ድሮው ስርአት ሊመልሱን” በሚል ዘግቶታል። ሰለዚህ በተለይ ሁለቱ በሂረሰቦች ከዚህ በላይ ለመታገስ አይችሉም። በማጠቃልያ የቀረበው መፍትሄ መሆን የሚገባው ቢሆንም በዎያኔ በኩል ተቀባይነቱ （ለስልት ካልሆነ በቀር）　እምብዛም ነው።ያው በዬፎረሙና ዊብሳይቱ እናገኘዋለን ስድቡንም ጭሆቱንም። የፉሺዝም ባህሪይ መደራደር ሳይሆን በአቋም እስከ መቃብር መውረድ ነው። ወያኔ የተለዬ ፋሺስት ይሆናል ብለን አንጠብቅም።

… Demeke